ይህንን ቁርአን ተጠባበቁት! የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ እርሱ (ቁርአን) ግመል ከታሰረችበት (ፈታ) ከምታመልጠው የበለጠ በጣም የሚያመልጥ ነው።

ከአቡ ሙሳ አልአሽዐሪይ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም እንዲህ አሉ:
"ይህንን ቁርአን ተጠባበቁት! የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ እርሱ (ቁርአን) ግመል ከታሰረችበት (ፈታ) ከምታመልጠው የበለጠ በጣም የሚያመልጥ ነው።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም አንድ ሰው ቁርአንን በልቡ ከሸመደደው በኋላ እንዳይረሳው ቁርአንን በመጠባበቅና በማንበቡ ላይ መዘውተርን አዘዙ። ቁርአን ከልብ ውስጥ ከታሰረች ግመል የበለጠ እጅግ የሚጠፋና የሚወገድ መሆኑን ነቢዩ ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም በመሀላቸው በማጠናከር ገለፁ። ግመል በክንዶቿ መሀል በገመድ ተጠፍራ ስታበቃ ሰውዬው ከተጠባበቃት ይይዛታል፤ ከለቀቃት ግን ትሄዳለችም ትጠፋለችም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5907